# ሰባቱ አብያተ ክርስትያናት (17)

## ጥናት አንድ (ራዕ 2:1-7)

የጥናት ዓላማ፡- እግዚአብሄር ሲገስጽና እንድንመቀስ ሲናገረን ንስሃ ገብቶ መመለስ የራሱ የሆነ በረከት እንዳለው በመረዳት ልባችንን እንዳይጠነክር ለማሳሰብ።
የምናሰላስለው ጥቅስ፡ «ንስሃም ግባ የቀደመውንም ሥራህን አድርግ... ድል ለነሳው በእግዚአብሄር ገነት ከለው ከህይወት ዛፍ እንዲበላ እሰጠዋለሁ።» ራዕ 2:5-7

1. «ሰባቱን ከዋክብት በቀኝ እጁ የያዘው፤ በሰባቱም የወርቅ መቅረዞች መከከል የሚመላለሰው..» በማለት በእጁና በእግሩ እየሰራ ያለውን መንገሩ ለኤፌሶን ቤ/ክ ከተናገረው ሃሳብ ጋራ እንዴት ይገናዘባል ትላለህ?
2. ኢየሱስ ስለ ኤፌሶን ቤ/ክ የሚያውቃቸው ነገሮች ምን ምን እንደሆኑ በመዘርዝር ተናገር።
3. ኢየሱስ ስለ ቤተ ክርስትያኒቱ እንደሚያውቅ የመሰከራቸውን ነገሮች በሙሉ ስትመለከት ሰዎች ስለዚህች ቤ/ክ ቢጠየቁ የሚሰጡት ሃሳብ ከኢየሱስ ጋራ በምን የለያይ ይመስልሃል?
4. በ2:4 ላይ የምነቅፍብህ ነገር አለኝ በማለት የሚጠቅሰው ነገር ምንድነው? በጣም ብዙ መልከም ነገር የሚታይባትን ቤ/ክ ለምንድነው አንዱን ነቀፋ ማጉላት ያስፈለገው?
5. ኢየሱስ የሚነቅፈውን ከነገረ በኋላ ቤተ ክርስቲያኒቱ እንድትወስድ የሚነግራት እርምጃዎች ምንና ምን እንደሆኑ ዘርዝር። እነዚህ እርምጃዎች ለማናቸውም መንገዱን ለሳተ ሰው ጠቃሚ መመሪያ በመሆን ሊያገለግሉ የሚችሉት እንዴት ነው?
6. ቤ/ክርስትያኒቱ ምክሩን ለመቀበልና ለመመለስ እንቢ ብትል የተሰጣትን ማስጠንቀቂያ ተናገር። አንድ ነገር ብቻ ለጎደለው ይህ አይነቱ ማስጠንቀቂያ አይበዛበትም ወይ? ለምን?
7. በቁጥር 7 መሰረት ኢየሱስ ለአብያተ ክርስትያናት የሚናገረውን ነገሮች እነማን እንዲሰሙ ነው የፈለገው? በዚህ ውስጥ እኛ ልንጠቃለል እንደምንችል የሚጠቁመው አባባል የትኛው ነው?
8. በዚህ ዐውደ ግብ መሰረት አንድን ሰው ድል ነሳ የሚያሰኘው ምን አድርጎ ሲገኝ ነው?
9. አንተስ በህይወትህ ጌታ በቃሉ ሲገስፅህ ንስሃ ገብተህ መንገድህን ለመቀየር ምን ያህል ዝግጁ ነህ? መታዘዝ የራሱ የሆነ በረከት ስላለው የበለጠ ለመትጋት ምክንያት አለንና እንበርታ።

# <u>ጥናት ሁለት (ራዕ 2:8-11)</u>

የጥናት ዓላማ:- መከራ በህይወታችን መጥቶ ህይወታችንን እንደማፅበል ሲያናውጠው፤ ድንገተኛነቱ ለእኛ እንጂ እግዚአብሄር ጅማሬውንና ፍጻሜውን የቀጠረለት ስለሆነ በእርሱ ማረፍን እንድንለማመድ ለመማር::

የምናሰላስለው ጥቅስ: **‹‹ዓስር ቀንም መከራ ትቀበላላችሁ። እስከ ሞት ድረስ ታማኝ ሁን፤ እኔም የህይወትን አክሊል እሰጥሃለሁ።››** *ራዕ* 2፥10

1. ራዕይ 2:8-11 ያለው ክፍል በአንድነት ይነበብ:: ጌታ የሱስ በዚህ ክፍል ምን በማለት ነው ራሱን ሲያስተዋውቅ የሚገኘው?
2. ኢየሱስ ራሱን ያስተዋወቀበት ሃሳብ ይህች ቤ/ክ ለምትገኝበት ሁኔታ መጽናናት ሊሆን የሚችልበትን መንገድ ታያለህ ወይ? አስረዳ::
3. ስለ ሰምርኔስ ቤ/ክ ጌታ አውቃለሁ የሚላቸው ሁለት ነገሮች ምን ምንድናቸው? በአንድ በኩል ድህነትህን አውቃለሁ ሲል በሌላ በኩል ደግሞ ሃብታም ነህ ይላል፤ እነዚህ ሁለት ሃሳቦች ይቃረናሉ ብለህ ታምናለህ ወይ? ካልሆነ ምን ማለቱ እንደሆነ አስረዳ::
4. ቁ9 ‹‹አይሁድ ሳይሆኑ አይሁድ ነን እያሉ...›› ይህንን አባባል እኛ ወዳለንበት ዘመን ብንተረጉመው ምን ማለት ሊሆን ይችላል? የዚህ ዓይነት ነገር በመሃላችንም እንደሚኖር መረዳት ለምን ይጠቅማል ብለህ እንደምታስብ ተናገር።
5. በቁ10 ላይ ለቤተክርስትያኒቱ የሚሰጣት ማስጠንቀቂያ ምንድነው? ክርስቶስ ኢየሱስ ቤተ ክርስትያኒቱ ልትገባ ያለችበትን ሁኔታ እያወቀ ከመጠቆም ይልቅ ለምን መከራው እንዳይመጣ አይከለክልላትም?
6. ይህ ከላይ የተነገረው መከራ ምንድነው? ይህንን ሁኔታ ከመምጣቱ በፊት አስቀድሞ ማስጠንቀቅ መቻሉና የቀኖቹን ብዛት መመደቡ ሰለርሱ ምን ይነግረናል?
7. በዚህ መከራ ውስጥ ስታልፍ ኢየሱስ ከቤተ ክርስትያኒቱ የሚጠብቀው ነገር ምንድነው? ከእርሱስ የሚጠበቅ ነገር አለወይ? ምንድነው?
8. ይህች ቤተ ክርስትያን ባለችበት ሁኔታ ወይም አውደ ምንባቡን በማየት ድል መንሳት የሚለው ሃሳብ የሚያመለክተን ምንን ነው?
9. ባላሰብክበት ጊዜና ሁኔታ መከራ መጥቶ አስደንግጦህ ያውቃል ወይ? ድንገተኛ የሚሆነው ለአንተ እንጂ ጌታህ አስቀድሞ ተጀምሮ የሚያበቃበትን ቀን የቀጠረለት መሆኑን ተረድተህ ጌታን አመስግን።

# ጥናት ሶስት (ራዕ 2:12-17)

**የጥናት ዓላማ:- በሃጥያታችን ንስሃ እንድገባ መንፈስ ቅዱስ ለልባችን ሲናገረን በቸልታ ማለፍ እንደማይኖርብንና የእግዚአብሄርን ትዕግስት ፍርድ እንደሚዘገይ አድርገን እንዳንረዳው ለማሳሰብ።**
**የምናሰላስለው ጥቅስ: ‹‹ስለዚህ ንስሃ ግባ፤ አለዚያ ቶሎ እመጣብሃለሁ፤ በአፌም ሰይፍ እዋጋቸዋለሁ።›› ራዕ 2:16**

1. ኢየሱስ ለዚህች ቤ/ክ ራሱን ያስተዋወቀው በምን መንገድ እንደሆነ ግለጽ:: ይህ ዓይነቱ አባባል ለጴርጋሞን ቤ/ክ ትክክለኛ መልዕክት የሚሆነው ለምንድነው?
2. ቤተ ክርስትያኒቱ ያለችበት ሁኔታ ከባድ መሆኑን እንደሚያውቅ ኢየሱስ ይናገራል:: ኢየሱስ ያለችበትን ሁኔታ ማወቁ በምን መንገድ መጽናናት ሊሆናት ይችላል? ለእኛስ?
3. የጴርጋሞን ቤ/ክ የሰይጣን መኖሪያ ተብሎ በመደጋገም በተነገረበት እየኖረ ነገር ግን የጌታን ስም ጠብቆ ይዟል:: የክርስቶስ ልጆች መኖር የሚችሉበትና የማይችሉበት ሥፍራ አለወይ? አማኞች የሚኖሩበት አካባቢ የመንፈሳዊ ህይወታቸውን ጥራት መቀየር አለበት ወይ? አስረዳ።
4. ቤተ ክርስትያኒቱን ኢየሱስ የሚነቅፍባቸው ሁለት ዋና ዋና ነገሮች ምንና ምንድናቸው?
5. የበለዓም ትምህርት በመባል በዚህ ክፍል የተጠቀሰው ትምህርት ምን እንደነበረ ግለጽ:: ዘኁ 24:13 ትና 25:1-3 ያለው ክፍል ይነበብና ተወያዩበት።
6. በዚህች ቤተ ክርስትያን ውስይ ስንት ዓይነት ሰዎችን ታያለህ?
7. በቁ16 ላይ ቤተ ክርስትያኒቱ እንታደርግ የምትጠየቀው ነገር ምንድነው? የተነገራትን ለማድረግ ፈቃደኛ ባትሆን ወጤቱ ምን ይሆናል?
8. በህይወትህ እንድታስተካክለው መንፈስ ቅዱስ አስጠንቅቆህ ያውቃል ወይ? ‹‹ ቶሎ እመጣለሁ›› ከሃጥያትህ እንድትመለስና እንድትታረም ሲታገስህ ስለማያውቅ ስላልሆነ ሲነግርህ ቸል ከማለት በቶሎ በንስሃ ምህረቱን ተለማመድ።

# ጥናት አራት (ራዕ 2:18-29)

**የጥናት ዓላማ:- በግላችንም ሆነ እንደ ቤተ ክርስትያን እግዚአብሄር እውነትን ሳንጥል ፍቅርንም ደግሞ ሳናቀዘቅዝ ሁለቱንም ሚዛናዊ በሆነ መንገድ ይዘን መራመድ እንደሚጠበቅብን ለመማር። የምናሰላስለው ጥቅስ: ‹‹*ሥራህን፤ ፍቅርህን፤ እምነትህን፤ አገልግሎትህንና ትዕግሥትህን አውቃለሁ።…ይሁን እንጂ የምነቅፍብህ ነገር አለኝ፤ ነቢይ ነኝ የምትለውን ሴት ኤልዛቤልን ችላ ብለሃታል።››* ኤፌ** 219-20

1. ራዕይ 2:18-19ን በማንበብ ኢየሱስ ስለ ትያጥሮን ቤ/ክ የሚያውቃቸውን እውነቶች በመዘርዘር ተናገር::
2. የቤተ ክርስትያኒቱ ዋነኛ ድክመት ሆኖ የቀረበው ነገር ምን ነበረ? ስለ ኤልዛቤል ከዚህ ክፍል የምናያቸው ነገሮች ምን ምንድናቸው?
3. በዚህች ሴት ላይ ኢየሱስ ስለወሰዳቸውና ሊወስድ ስላለው እርምጃዎች ተናገር:: ለኤልዛቤል የንስሃ እድል መስጠቱ ምን ያስተምረናል?
4. ኤልዛቤልን አስመልክቶ በትያጥሮን ቤ/ክ ሁለት ዓይነት አማኞች ይታያሉ:: እነዚህ እነማን እንደሆኑ አስረዳ::
5. በቁ 23 ላይ የኤልዛቤል ልጆች አድርጎ የሚናገራቸው እነማንን ነው? እነዚህን ልጆች በመግደል እግዚአብሄር ለአብያተ ክርስትያናት በሙሉ ሊያስተምር የሚፍልጋቸው ትምህርቶች ምን ምንድናቸው?
6. «ሌላ ሸክም አልጭንባችሁም» ቁ 24 ከዚህ አባባል ስለ ጌታ ባህርይ ልንማር የምንችለው አንድ እውነት ምንድነው? ሰዎች ስለርሱ ከሚሰነዝሩት አስተያየት ይህ የሚለየው በምን መንገድ ነው?
7. «ነብይ ነኝ የምትለውን» ቁ 20 ነብይ ነኝ የሚሉትን ሰዎች ማድረግ ስለሚገባን ጥንቃቄ ከዚህ ክፍል ልንማረው የምንችላቸውን ነገሮች ዘርዝር::
8. ይህች ቤተ ክርስትያን ከኤፌሶን ቤተ ክርስትያን የምትለይበትን አንድ ዋነኛ ነገር ተናገር:: (ኤፌሶን ዶክትሪንን ትመረምራለች)
9. ኤፌሶን ዶክትሪን ይዛ ያለፍቅር የምትጓዝ ስትሆን ይህች ቤ/ክ ደግሞ ፍቅር ይዛ ያለ ዶክትሪን የምትጓዝ ነች:: በዚህ መነጽር ህይወትህን ስትመለከተው የትኛውን ይመስላል? ጌታ የሚጠብቅብን ሚዛን ያለው ህይወት መምራት መሆኑን ዘወትር በአዕምሮህ አኑረው::

# ጥናት አምስት (ራዕ 3:1-6)

**የጥናት ዓላማ:- ሕይወታችንን ልንመዝንበት የሚገባን ትክክለኛ ሚዛን የእግዚአብሄር ሚዛን ማለትም የእግዚአብሄር ቃል እንጂ ሌላ ሚዛን በእርሱ ዘንድ ተቀባይነት እንደማይኖረው ለመማር።**

**የምናሰላስለው ጥቅስ: ‹‹ስለዚህ ንቃ፤ ሊሞት የተቃረበውን የቀረውን ነገር አጽና፤ ሥራህ በአምላኬ ፊት ፍጹም ሆኖ አላገኘሁትም።›› ራዕ** 3፡2

1. የሰርዴስ ቤተ ክርስትያን በሰዎች ዓይን የምትታይበትን ሁኔታ ምን ይመስላል? በኢየሱስ ዓይንስ? በሁለቱ አመለከከቶች መሃል ለምን ይህንን ያህል ርቀት ሊኖር የቻለ ይመስልሃል?
2. በቁጥር 1 ላይ ሞተሃል እያለ በቁጥር 2 ላይ ደግሞ እንዲነቃ ያስጠነቅቀዋል:: ከዚህ አንጻር ስትመለከተው ሞተሃል የሚለውን አባባል በምን ትረዳዋለህ?
3. በቁጥር 2 ላይ ነቅቶ እንዲያከናውን የተነገረው ነገር ምንድነው? በዚህ ክፍል መሰረት በህይወታችን ሊሞቱ የደረሱ ነገሮችን መልሶ ለመስራት የሚያስፈልገን አንድ ነገር ምንድነው?
4. ሰዎች ስንባል ሰው ስለኛ የሚናገረውን ነገር ትልቅ ስፍራ እንሰጠዋለን:: ቁ2ትን ስናነብ **በኢየሱስ አመለካከት የሰው ሥራ የሚመዘነው በማን ሚዛን ነው? ከዚህ ሃሳብ በመነሳት** በህይወታችን መለወጥ የሚገባን አመለከከት ምንድነው?
5. በቁጥር 3 መሰረት ከእግዚአብሄር ቃል በምንሰማውና በተቀበልነው እውነት ላይ ሊወሰዱ የሚገባቸው ተጨማሪ እርምጃዎች ምን ምን እንደሆኑ ተናገር::
6. ቤተ ክርስትያኒቱ የተሰጣትን ማስጠንቀቂያዎች ችላ ብትልና ባትነቃ የሚከተለው ነገር ምንድነው?
7. ቁጥር 4 በሰርዴስ ቤ/ክ የሚገኙት ቅዱሳን በሁለት የከፈለበት መንገድ ምን እንደሆነ አስረዳ:: አብዛኛው የሚሄድበትን መንገድ ስለመከተል ከዚህ ክፍል ምን እንማራለን?
8. በዚህ ዐውደ ግብ መሰረት አማኝ ድል ነሳ ማለት ምን ማለት ነው?
9. ህይወትህን የምታስመዝነው በሰዎች ወይስ በእግዚአብሄር ዓይን? ዋጋህ ዘላለማዊ እንዲሆን ከፈለግህ ከሰው ይልቅ በእግዚአብሄር ላይ ዐይንህን አድርግ::

# ጥናት ስድስት (ራዕ 3፡7-13)

የጥናት ዓላማ፡- ጌታ በህይወታችን ይሁን ያለውን ማናቸውንም ነገር ሊያስቀር የሚችል ማንም እንደሌለ፤ እንዲሁም አይሆንም ያለውን ነገር ማንም እንዲሆን ሊያደርግ እንደማይችል ለመማር። የምናሰላስለው ጥቅስ፡- ‹‹እርሱ የከፈተውን ማንም ሊዘጋ አይችልም፤ የዘጋውንም ማንም ሊከፍተው አይችልም።›› ራዕ 3፡7

1. ኤፌ 3፡7-13 በአንድነት ይነበብ:: ይህ ክፍል ኢየሱስን የሚያስተዋውቅባቸው ሶስት ነገሮች ምን ምን እንደሆኑ በዝርዝር አስረዳ::
2. ስለዚህች ቤተ ክርስትያን ኢየሱስ አውቃለሁ የሚላቸውን ነገሮች ምን ምንድናቸው?
3. ኢየሱስ ራሱን ካስተዋወቀበት እውነት ጋራ በማየት፤ ለፊላደልፊያ ቤተ ክርስትያን የተከፈተው በር ሊዘጋ የማይችልበት ምክንያት ለምንድነው?
4. ቁ8 ‹‹ሃይልህ ትንሽ እንደሆነ አውቃለሁ፤ ሆኖም ቃሌን ጠብቀሃል።›› ይህ አይነቱ እውቀት ለእያንዳንዳችን መልካም ዜና የሚሆንልን ምክንያት ለምንድነው? በክርስትና ህይወት ውስጥ ሃይል ትንሽ ሆኖ ነገር ግን ቃሉን መጠበቅ የሚቻለው እንዴት ነው?
5. በቁ7-10 ውስጥ ኢየሱስ ለዚህች ቤተ ክርስትያን ያደረጋቸውና ሊያደርግላት ቃል የሚገባቸው ቢያንስ ሶስት ነገሮችን ተናገር። ቤተ ክርስትያኒቱ ደግሞ እንዳደረገች የሚነገርላትን ሶስት ነገሮች ከዚሁ ክፍል በመነሳት ተናገር።
6. በቁ11 ላይ ለፊላደልፊያ ቤተ ክርስትያን ምን እንድታደርግ ነው የሚያበረታታት? ለዚህስ ተጨማሪ ማበረታቻ አድርጎ የሚነግራት እውነት ምንድነው?
7. ራዕ 3፡12-13 ያለው ክፍል በአጠቃላ የሚናገረው ምንን በተመለከተ ነው? በዚህ ክፍል ውስጥ ድል የነሳ የሚሆንለት ነገሮች ምን ምን እንደሆነ አንድ በአንድ በመዘርዘር ተናገር።
8. እርሱ የከፈተውን መዝጋት ወይም የዘጋውን መክፈት ማንም እንደማይችል ማወቅህ ለህይወትህ ምን ጥቅም ይኖረዋል? ጌታ በህይወትህ ይሁን ያለው አይቀርም፤ አይሁን ያለው ደግሞ አይሆንምና በዚህ ተጽናና።

# ጥናት ሰባት (ራዕይ 3፡14-22)

የጥናቱ ዓላማ፡- በገዛ ቤተ ክርስትያኑ ንጉስና ባለቤት ሆኖ በመሪነት ሊመላለስ ሲገባው፤ በተለያዩ ነገሮች ቤቱን በመሙላት ኢየሱስ የማይገኝበት ጉባኤ ይዘን ልንቀመጥ እንደምንችል ለመማር። የምናሰላስለው ጥቅስ፡- ‹‹እነሆ በደጅ ቆሜ አንኳኳለሁ፤ ማንም ድምጼን ሰምቶ በሩን ቢከፍትልኝ ወደ እርሱ ገብቼ ከእርሱ ጋራ እበላለሁ፤ እርሱም ከእኔ ጋራ ይበላል።›› ራዕ 3፡20

1. ራዕ 3፡14-22 በአንድነት ይነበብ። ጌታ የሱስ ለዚህች ቤተ ክርስትያን ራሱን ያስተዋወቀበት አራት ስሞችን አንድ በአንድ ተናገር።
2. ይህች ቤተ ክርስትያን የክርስትና ተኩሳቷ ሲለካ ምን ይመስላል? ትኩሳቷ የተለካውስ በማን ነው?
3. ኢየሱስ ክርስቶስ ‹‹ቀዝቃዛ ወይም ትኩስ ብትሆን በወደድሁ ነበር።››ሲል የህይወት ቅዝቃዜንም እንደ ትኩሳት ይወዳል ለማለት ነው? ካልሆነስ ምን ለማለት ፈልጎ ነው?
4. በቁ17 መሰረት ሎዶቅያ ራሷን በምታይበትና ኢየሱስ በሚያያት መካከል ያለውን ልዩነት ተናገር። እኛ ለራሳችንን ሊኖረን ስለምችለው አመለካከት ይህ ክፍል ምን ሃሳብ ይሰጠናል?
5. ኢየሱስ የቤተ ክርስትያኒቱን የአመለካከት ድክመቷን ለማረም እንድትችል በቁ18 ላይ የሰጣት ምክር ምን ነበረ?
6. በቁ19 ላይ ከምናነበው፤ ለሎዶቅያ ብቻ ሳይሆን ለሁሉም ያስተላለፈው የተግሳጽ ቃል ከምን የመነጨ እንደሆነ ነው የምናየው? ከዚሁ ቁጥር ሎዶቅያ እንድትወስዳቸው የተነገሩት ሁለት እርምጃዎች ምንና ምንድናቸው?
7. ቁ20ን ስንመለከት ኢየሱስ ክርስቶስ በዚህች ቤተ ክርስትያን ውስጥ ስላለው ሥፍራ የሚያሳየን ነገር ምንድነው?
8. ህይወትህ ኢየሱስ ተመችቶት እንደ ጌታነቱ የሚገዛበት ወይስ በቤቱ የሚለምንበት? በገዛ ህይወትህም ሆነ በቤተ ክርስትያንህ በዚህ ዓይነቱ ውድቀት እንዳትወሰድ ጥንቃቄ አድርግ።